ታህሳስ 26/2004 ዓ.ም.

# በደቡብ ኢትዮጵያ መኢአድ ስድስት አባላቱ በገዥው ፓርቲ ታሠሩበት፡፡

በደቡብ ኢትዮጵያ በጎፋ ልዩ ዞን በደምባ ጎፋ ወረዳ ስድስት የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) አመራር አባላት ታህሳስ 23/2004 ዓ.ም ጀምሮ በገዥው ፓርቲ በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን አቶ እንድርያስ ኤሮ የመኢአድ ማዕከላዊ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልና የደቡብ ቀጠና ኃላፊ ለመኢአድ ህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ገለጹ፡፡ አቶ እንደርያስ ኤሮ

1. አቶ አንድነት ኦዳ - ከመሃል ከብዛ ቀበሌ፣ የደምባ ጎፋ የመኢአድ የህዝብ ግንኙት ኃላፊ፣

2. አቶ መዝገበ እመጣለሁ - የመሃል ከብዛ ቀበሌ የአመራር አባል፣

3. አቶ መስቀሌ ጮፎ - የመሃል ከብዛ ቀበሌ የአመራር አባል፣

4. አቶ ዙቤራ ሱማ - የጫላ ፀላ በና ቀበሌ የአመራር አባል፣

5. አቶ ቱንጋ ቱቡሌ - የያለው አሊዛ ቀበሌ የአመራር አባል እና

6. አቶ ዞመራ ዞምባ - የያለው አሊዛ ቀበሌ የአመራር አባል በገዥው ፓርቲ አባላት ተይዘው ደምባ ጎፋ ፖሊስ ጣቢያ የታሠሩ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡ የመኢአድ አባላት የታሰሩት ልማት አደናቃፊዎች በሚል ውንጀላ እንደሆነም አቶ እንድርያስ ጠቅሰዋል፡፡ታሳሪዎች ከሚኖሩበት አካባቢ 55 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ሳውላ ከተማ በመሆኑም ስንቅ ለማቀበል ለቤተሰቦቻቸው አስቸጋሪ መሆኑንም ጨምረው ተናግረዋል፡፡ የመኢአድ የደቡብ ቀጠና ኃላፊ ማብራሪያቸውን ሲቀጥሉም አባሎቻችን 55 ኪሎ ሜትር እርቀት ተጉዘው እንዲታሰሩ የተደረጉት በብጣሽ ወረቀት ትዕዛዝ መሆኑና አቶ ዙቤራ ሱማ እስረኞቹን ለመጠየቅ ፖሊስ ጣቢያ በመሄዳቸው እንዲታሠሩ መደረጋቸው የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች ለመኢአድ አባላት ያላቸውን ጥላቻ የበለጠ ያሳያል ብለዋል፡፡

አቶ እንደርያስ ኤሮ የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች የመኢአድ አባላትን ልማት አደናቃፊዎች ቢሏቸውም ልማት አደናቃፊዎች አለመሆናቸውን ካስረዱ በኋላ በካድሬዎች ትዕዛዝ የግለሰብን ቦታ ሄዶ መቆፈር የሰዎችን መብት መድፈር በመሆኑ የመኢአድ አባላት አቋም ወስደው ለአካባቢው አስተዳደርም የግለሰብን ማሳ የማይቆፍሩ መሆናቸውን ማሳወቃቸውን ገልጸዋል፡፡